

ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ.
DEBO MICROFINANCE INSTITUTION S.C.

ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ
የባለአክሲዮኖች 11ኛ መደበኛ ጠቅላላ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367 (1)፣ 370 እና 371(1) እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 18 መሠረት የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 11ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 15 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት እስከ 11:30 ሰዓት በአዲስ አበባ አያ ሆቴል /AYA Hotel / የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳል::

በመሆኑም የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰዉ ቀን፣ሰዓትና ቦታ በጉባዔው ላይ እንዲትሳተፉ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል::

1. አክሲዮን ማህበሩን የሚመለከቱ መረጃዎች

1.1 የማህበሩ ስም፡- ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ

1.2 የማህበሩ ዓይነት፡ በማይክሮ ፋይናንስ ስራ ላይ የተሰማራ አ.ማ

1.3 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቢሮ ቁጥር 111 ቲኬ ሕንጻ

1.4 የአክሲዮን ማህበሩ ድህረ ገፅ፡ WWW.debomicrofinance.com

1.5 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡ MT/AA/3/0041241/2010

1.6 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል፡ ብር 100,000,000

1.7 የተከፈለ የማህበሩ ካፒታል፡ ብር 100,000,000

2. የ11ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1 በቀረቡት የጉባዔ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.2 አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የአክሲዮን ዝውውር ማፅደቅ፣

2.3 እ.አ.አ የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.4 እ.አ.አ የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የውጭ አዲተሮች ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.5 እ.አ.አ የ2024/2025 ሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አመዳደብና ክፍፍል ላይ መወያየትና መወሰን፣

2.6 ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚከፈል ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ላይ መወያየትና መወሰን፣

2.7 ለ2018 ዓ.ም የውጭ አዲተሩን እንደገና መሾምና ክፍያውን በመወሰን ማፅደቅ፣

2.8 የጉባዔዉን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው::

3. ማሳሰቢያ

3.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋና መ/ቤት ቢሮ ቦሌ ቲኬ ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 111 በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካይም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ በመሆን ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን:: ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉበኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

3.2 ባለአክስዮኖቹ እና የባለአክሲዮን ተወካይ በጉባዔው ሲገኙ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና የፋይዳ መታወቂያ ዋናውን ከኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል::

የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር

የዳይሬክተሮች ቦርድ

30 ዓመት
የእሑድ እትም
መስከረም 18 ቀን 2018
ቅዳሜ 31 ቁጥር 2652 | ጳጉሜን 6 ቀን 1987 ተመሠረተ | ዋጋው ብር 50.00
ትኩስና ተጨማሪ መረጃዎችን በድረ ገጻችን ያገኛሉ www.ethiopianreporter.com